በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# እውነተኛዪቱ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? - ክፍል አንድ

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት
የካቲት ፲፩ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# መግቢያ

- በርካታዎች በራችን ሲንኳኳ ከፍተን አለባበሳቸው የተለየ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎችን እጅ ከነሳን በኋላ የዎች ታወር ሕትመቶች የሆኑ መጽሔቶችን ተቀብለናል፡፡ ብናነጋግራቸው #የይሖዋ ምስክሮች; እንደሆኑ እንረዳለን፡፡

- ውይይታችንንም ብንቀጥል በ#ሰንበት; በ #አዳራሻቸው; አምልኮታቸውን የሚፈጽሙ መሆናቸውንና እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያንም እንደሆኑ ያስረዱናል፡፡ ነገር ግን እውነተኛይቱን ቤተክርስቲያን ሊሆኑ ይችላሉ?

- አንዳንድ ጊዜም በአለባበሳቸው የምንለያቸው #ዘናጭ; የሆኑ በአገልግሎት ላይ ነን የሚሉ #የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤ/ክ - ሞርሞን; ተከታይ ወጣቶች ሊገጥሙን ይችላሉ፡፡ እነርሱም ትክክለኛይቱ ቤ/ክ እኛ ነን ይሉናል፡፡ ነገር ግን እውነተኛይቱን ቤተክርስቲያን ሊሆኑ ይችላሉ?

- በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የፕሮቴስታንቶች የተሃድሶ እንቅስቃሴ ወቅት አንዱ ጥያቄ እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን እንዴት ትታወቃለች? የሚል ነበር፡፡ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ራሷን እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን እንደሆነች ለማሳመን የተቻላትን ሁሉ ተጽእኖ አድርጋለች፡፡

- እውነተኛይቱ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ማናት እንዴትስ ትታወቃለች?

# መግቢያ…

- በሃይማኖት ስም የሚንቀሳቀሱ #አብያተ ክርስቲያናት;ና የክህደት ትምህርቶች መበራከት እውነተኛይቱን ቤ/ክ ለይቶ ማወቅን አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ ነገር ግን ባለንበት ዘመንም ቢሆን እውነተኛይቱ ቤ/ክ አንዲት ብቻ ናት፡፡

- አንዳንዶች #የቀደመችው ሐዋርያዊት ቤ/ክ በሂደት ተበታትና አሁን ከቀደመው መንፈሳዊ ሀብታቷ፣ ቅድስናዋ፣ እና እውነት ሽርፍራፊው ብቻ የሚገኝባት መሆኑን; ይናገራሉ፡፡ #በስምምነትና በጋራ መግባባት መልሳ እንደገና መመስረት ትችላለችም; ይላሉ፡፡ ይኸም ሁልጊዜ በኤኩሚኒዝም (WCC) ሲንጸባረቅ የኖረ ነው፡፡ ግን ጌታችን በደሙ አንድ ጊዜ የመሰረታት ቤ/ክ እንደገና ከሁሉም አቋም አንዳንዱ እየተለቀመ ሌላ መሠረት እንዳስፈለገው ቤት ተመስርታ እውነተኛይቱን ቤ/ክ መሆን ትችላለች? መጽሐፉን የሚያነቡትና የማያምኑት ስለሚበረክቱ … *የሐ. ሥራ 20 ፥ 28*

- ይኸ ሁሉ የተምታታ አመለካከትና የተሳሳተ ሐሳብ ምንጩ ጌታችን ስለሰው ድኅነት ያስተማረውን ትምህርት በአግባብ አለመረዳት ነው፡፡ ጌታችን ባስተማረው ትምህርት፤ በወንጌላት፤ በመልዕክታት ሰው የራሱን ነፍስ ማዳን እንደማይችል የሰውን ዘር ሁሉ ለማዳን እግዚአብሔር ሰው ሆኖ እንደመጣ ተነግሮናል፡፡

# የእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን መታወቂያ ባሕርያት

- በዘመነ ሐዋርያት አንዲት ቤተ ክርስቲያን ነበረች። በሐዋርያት ሥራ እንደተገለጸው ከጌታችን ትንሣኤ በኋላ በሃምሳኛው ቀን በአንዲቱ ቤተክርስቲያን ተሰብስበው ሲጸልዩ መንፈስቅዱስን በእሳት አምሳል ወርዷል። የሐ. ሥራ 2፤1-47፡ የሐ. ሥራ 12፤12

- ከዚያ ጀምሮ የክርስትና እምነት እየተስፋፋ ሄደ፤ አብያተ ክርስቲያናቱም በቦታ ቢራራቁም ሁሉም የአንዲት ቅድስትና ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን አካል ነበሩ። -

- ያቺም ቤተክርስቲያን አንድ ሃይማኖት፤ አንድ ዓይነት ምስጢራት (ጥምቀት፤ ቁርባን...) ነበራት። ምስጢራቱንም የሚፈጽሙት ሐዋርያት ነበሩ። አገልግሎቱ እየሰፋ ሲሄድ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቁ የሆኑ ጳጳሳት፤ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሾሙ። ሐዋርያት ጳጳሳቱ ሁሉ ኃላፊነታቸውን ንጹሕ የሆነውን የክርስትና ትምህርት በመከተል በመንፈሳዊነት በመኖር እንዲፈጽሙ፤ ጳጳሳትን ቀሳውስትንና ዲያቆናትን እንዲሾሙ አዘዟቸው።

- ቤተክርስቲያንም በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ብዙ ቅርንጫፎች እንዳሉት ዛፍም በየአገሩ ሁሉ በትምህርተ ሃይማኖት፤ በቤተክርስቲያን አገልግሎት፤ በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲሁም በመንፈሳዊ መዝሙራት፤ በሥነ ሕንጻ፤ በሥዕል፤ ... እውነተኛይቱን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን መልክ እንደያዘች ትውፊቷን እንደጠበቀች አደገች ተስፋፋችም።

# የእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን መታወቂያ ባሕርያት...

- ወንጌላቱና መልዕክታቱ ወዲያው ወይም በዚያው ወቅት ተቀድተው አልተሰራጩም። ቤተክርስቲያን ከተመሰረተች በኋላ ለረጅም ዘመናት የትምህርት ምንጩ መጽሐፍ ቅዱስ ስላልተጠረዘ ትምህርቱ በጽሑፍ ሳይሆን ሐዋርያት ራሳቸው እንደተናገሩት በትውፊት የተላለፈ ነበር። ትውፊቱም ራሱ የእውነተኛ ሃይማኖት ትምህርት ነበር።

- በቤተ ክርስቲያን በሃይማኖትም፤ በአስተዳደርም ሆነ በምስጢራተ ቤ/ክ ... የሚነሱ ጉዳዮች የሚታዩት ሐዋርያት ከጌታችን ተምረው ባወረሱት (ባቀበሉት) ትምህርትና ሥርዓት ነበር። ይህም ትውፊት ይባላል። ቅብብል ማለት ነው። ከዚህ የወጣው ሁሉ ሐሰት እንደሆነ ተቆጥሮ ይወገድ ነበር።

- ይህም የሐዋርያት ትውፊት ተጠብቆ በጥንቷ ቤተክርስቲያን የነበሩ አባቶች ክርስቲያናዊ የሆኑትን ጽሑፎች ሁሉ በጥንቃቄ በመመርመር የሐዋርያትን ሥራዎች ሁሉ ሰበሰቡ። በአንድነትም አድርገው አዲስ ኪዳን ብለው ሰየሙት። ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም ጋር አድርገው ዛሬ በቤተክርስቲያናችን የምናገኘውን መጽሐፍ ቅዱስ ጠርዘው ሰጡን።

- ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው ከቤተክርስቲያን ውስጥ መሆኑንና ቤ/ክ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘች ሳትሆን በክርስቶስ ደም የተመሠረተችና በሐዋርያት ትምህርት የተስፋፋች መሆኗን ጠንቅቀን ማወቅ ይገባናል።

## የእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን መታወቂያ ባሕርያት…

- የሐዋርያቱ ተከታዮች ለሆኑ የትምህርታቸውንም አንድምታ ትርጉም ለጻፉልን ለአበው ሐዋርያቱ ምስጋና ይግባና ከፍተኛ ዋጋ ያለውን የመጀመሪያይቱን ቤተክርስቲያን ሕይወትና ሃይማኖት በአግባብ ለማወቅ ችለናል፡፡

- በዚያ ዘመን በአንዲቱ ቅድስትና ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን የነበረው እምነት ዓለምአቀፋዊ ነበር፡፡

- ቤተ ክርስቲያን በዚያ ዘመን የራስዋ የሆኑ መታወቂያዎች ነበራት ብሎ መቀበል የግድ የሚታሰብ ነው፡፡ በፍቅር ማዕድ፤ በቅዱስ ቁርባንና በቅዳሴ፡ በጳጳሳት፤ በቀሳውስትና በዲያቆናት አገልግሎት፤ በጸሎት፡ ሥግደትና የመዝሙር ሥርዓት፤ በቀኖናዋ፤ አብያተ ክርስቲያናቱ በሚኖራቸው ግኑኝነትና በማኅበራዊ ሕይወት … ሳይቀር የራስዋ ልዩ መታወቂያ (Identity) ነበራት ያም ከአባቶች ወደ ልጆች እየተላለፈ እስካሁን ይኖራል፡፡

- ይሁን እንጂ ከዚህ ንጹሕ ከሆነ ሐዋርያዊ ትምህርትና ትውፊት በመለየት ክህደትን የሚዘሩ ማቆጥቆጥ የጀመሩት ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ ነበር፡፡ ይህንም አስመልክቶ ሐዋርያት #ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን፡፡; *ገላትያ 1፤8* በማለት ከጌታችን ከተማሩት መንገድ የወጣውን እንዳይከተሉ አስጠንቅቀዋል፡፡

# *የእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን መታወቂያ ባሕርያት…*

- የሐዋርያት ተከታዮች ለሆኑ ክርስቲያኖች ሁሉ ለድኅነታቸው የቤተክርስቲያንን አስፈላጊነት በተመለከተ ምንም አከራካሪ ጉዳይ አይኖርም፡፡

- ቤተ ከርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት፡፡ #… ለቤተክርስቲያን ሰጠው፤ እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት፡፡;ኤፌ 1፤21-23፡፡ ቤተክርስቲያን ምዕመናን በሕይወት ባሕር እየቀዘፉ ወደ ዘላለማዊት መንግሥት ወደብ የሚደርሱባት የኖኅ መርከብ ናት፡፡ ቤተክርስቲያን ከሰው ሁሉ ምልከታ በላይ ከፍ ያለች፤ መንገደኞችዋን ሁሉ ወደእግዚአብሔር፡ ቅዱሳንና መላእክት አንድነት ወደ ሰማያዊ መንግሥት የምትመራ ከፍ ያለች ተራራ ናት፡፡

- በክርስትና የመጀመሪያዎች ዘመናት በክርስቶስ እንዲሁም በምድር በሠራው ሥራ ማመን ፤ ይህ ስጦታ በሰይጣንም ፈጽሞ መወገድ በማይችልበት መልኩ ላመኑበት ሁሉ የቤ/ክ ሀብታት ስለመዳናቸው የተሰጡ ስጦታዎች ነበሩ፡፡

- የብሉይ ኪዳን ነቢያት፤ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችንና፤ ደቀመዛሙርቱ ቤተክርስቲያን እስከ ዓለም ፍጻሜ የምትኖር መሆንዋን በግልጽ አስተምረዋል፡፡ ዳንኤል 2፡44 ፤ #የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም፡፡; ማቴዎስ 16፡18

- ጌታችን በገባልን ቃልኪዳን ካመንን ቤተክርስቲያኑ በኛ ዘመን ከዚህም በኋላ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የምትኖር መሆንዋን እንመን፡፡ *2ኛ ተሰሎንቄ 2፡4*
*ታዲያ በየት ትገኛለች? ማንስ ተብላ ትጠራለች?*

# ይቀጥላል።

# ወስብሐት

# ለእግዚአብሔር።